# በአንድ ፍላጻ ሶስት ሚዳቋ ፡-

# ምስክርነት ከወንጀለኞች አንደበት???

(በህያዉ ቃል)

ክፍል አንድ

፩

የትም ይሁን የት ፡ የማይበርድ የደም ጥም የሚያቅነዘንዛቸዉ ወሮበሎች በተሰባሰቡበት ዝግ ስርአት ዉስጥ የሽብር ጥቃት ዒላማ በተደረጉ የሕብረተሰብ አባላት ላይ የሚፈጸም አረመኔያዊ ተግባር "ወንጀል" በሚለዉ የጅምላ ቃል መፈረጅ ያንሰዋል።ቢያንስ ቃሉ በሽብሩ ሰለባዎች ላይ የደረሰዉን የስነልቡናም የአካል ስቃይ ያሳንሳል--ያለሳልሳል። ሕግን ከነማስፈጸሚያዉ ጠቅልለዉ እጃቸዉ የሚያስገቡት እነዚህ ሐይሎች "ጠላት" ባሏቸዉ ወገኖች ላይ የሚፈጽሟቸዉ ድርጊቶች ከግፍ በላይ ፡ ከጭካኔም ተግባራት ያለፉ ፡ የሰዉን ልጅ ሞራላዊ ደንቦች ከስር መሰረታቸዉ የሚንዱ ናቸዉ። በቃል ወይም በቃላት ሲመነዘር ደግሞ መጠን የለሹ "ግፍ "ወደተራ ስታትስቲክስነት ያዘቀዝቃል።

ሁለተኛዉ የዓለም ጦርነት ሊፈጸም ጥቂት ቀናት ብቻ እንደቀሩት ቀንደኛዉ ናዚ አዶልፍ ኤክማን መሰሎቹን ሰብስቦ "የአምስት ሚሊዮን አይሁዶች ወይም የመንግስታችን ጠላቶች ሞት እዉን ሆኖ በሕሊናዬ በመቀረጹ እጅግ በጣም ረክቻለሁ ፡- እናም በሳቅ እየተፍነከነከሁ ነዉ ወደመቃብሬ ዘልዬ የምገባዉ፡" በማለት የተለመደ ጉራዉን ነዝቶ ነበር። የአፉ አልያዘለትም። ብዙም ሳይቆይ የጀርመን ሠራዊት ተፈታ ።አዶልፍ ኤክማንም በተጭበረበሩ የይለፍ ወረቀቶች ታግዞ እግሬ አዉጪኝ አለ ። ሪካርዶ ክሌመንት በሚል ስም የቦነስ አይረስ ከተማ ነዋሪ ሆኖ የወገኖቻቸዉን ደም በማያስቀሩት እስራኤላዉያን እጅ እስከወደቀባት ግንቦት 1968 ዓ.ም. ድረስ ኖረ።

ኤክማን በተያዘበት ወቅት ወደእስራኤል ለመወሰድ ፈቃደኛነቱን በፊርማዉ አረጋግጧል ፡(የእስረኛ ቅንጡ ፡ ባይፈቅድስ መሄድ ሊቀርለት ኖሯል?) ። ለምን እንደፈረመ ተጠይቆ የሰጠዉ ምላሽ ግን ሊጠቀስ የሚገባዉ ነዉ። "በመጨረሻዉ ከገዛ ራሴ ጋር ሰላም ማዉረድ እሻለሁ ፡" ነበር ያለዉ ። ግንቦት 23 ቀን 1970 ዓ.ም ከመንፈቀ ሌት በፊት ካንገቱ ገመድ ሲገባለት ምን ያህል ይህ ምኞቱ እንደሰመረለት አይታወቅም ። ሬሳዉ ግን ተቃጥሎ አመዱ ከእስራኤል ድንበር ዉጭ ፡ በሜዲቴራኒያን ባሕር ላይ ተነስንሷል።

ናዚ ጀርመንና ባለስልጣናቷ ከቶም የዚህ ጽሁፍ ዓላማ አይደሉም ። ብዙዎቹ በታሪክ ዉስጥ ለሁሌዉ ሲጠቀስ በሚኖር መልኩ ከየተሸሸጉበት ስፍራ በወረንጦ እየተለቀሙ ርዕሰ ሀያላኑ መንግስታት በሰየሙት ሸንጎ በተከሳሽነት ቆመዉና ጠበቃ ተከራክሮላቸዉ ፡- የዘሩትን ያህል ባይሆንም በሰብአዊነት የተለሳለሰ ፍርድ የወሰነባቸዉን ያህል አጭደዋል።ኤክማን ተለይቶ መጠቀሱም ሌላ ፋይዳ ኖሮት አይደለም። ይልቁኑ ሰብአዊነትን በመጋፋት በሰዎች ህይወትና ክብር ላይ የሚፈጸሙ የግፍ ተግባራት በአፈጻጻማቸዉ ምን ድንበር ቢያራርቃቸዉ እንኳዋ ህሊናን በማሰቀቅ ደረጃ መሳ ለመሳ በመሆናቸዉ ምናልባት የምንቀስመዉ ጉዳይ አይታጣምና አጉልቶ ለማሳዬት ሲባል ብቻ ነዉ።እንጂማ የራሳችንን ጠያይም ኤክማኖች በአካል በግብር ያስተዋልን መሆናችን ለመቼዉም አይዘነጋም።

እንደሚታወቀዉ ከ1960ዎቹ ዓመታት መጋመሻ ወዲህ ኢትዮጵያ ዉስጥ ለማህበራዊ ስርዓት ለዉጥ የተካኼደዉ ትግል ዘዉዳዊዉን አገዛዝ ከሀገራችን መልክዐ ፖለቲካ እስከወዲያኛዉ ለማሰናበት በቅቷል ።ይሁን እንጂ በምትኩ በዜጎች ፈቃድ የሚመራ የፖለቲካ ይትበሐል ለመመስረት አልታደለም ። በመሆኑም በሕዝብ ላይ ተጭነዉ እንዳሻቸዉ በጉልበት የሚገዙ አምባገነኖች እስከዛሬ ድረስ በመንበረ ሥልጣኑ ላይ እየተፈራረቁበት ይገኛሉ። እስከአሁን በዘለቁት ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ዉስጥ ሕዝቡ አሜን ብሎ የተገዛበት አንድም ወቅት የለም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከየአቅጫዉ ለተሻለ ህይወትና ለሥርዓት ለዉጥ ያደረጋቸዉ ትግሎችና እንቅስቃሴዎች ያልተቀናጁ ፡-የሚያስፈልገዉን ያህልም ያልተደራጁ በመሆናቸዉ ሳቢያ ለተመኘዉ ዉጤት አላበቁትም ።ይልቁኑ ሥልጣናቸዉን ሙጥኝ ያሉ ወታደራዊና የስቪል ገዥዎች በሀይል ጨፍልቀዋቸዋል።

ወታደራዊዉ መንግስትና በዙሪያዉ በፈቃደኛነትም ሆነ በቅጥረኛነት የተኮለኮሉ ነብሰበላዎች በአባሪ ተባባሪነት በደርግ አገዛዝ ላይ የተቀጣጠለዉን ሕዝባዊ ተቃዉሞና ቁጣ ከስረመሠረቱ ለመደምሰስ ከ"አብዮታዊ ርምጃ "እስከ "ቀይ-ሽብር "ያካሄዱት መንግስታዊ ሽብርና ፍጅት የሕግን ልዕልናና የሞራልን ደንቦች ያፈረሰ ፡- ከዚያ በፊት ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ በዜጎች ላይ በአዋጅ የተካኼደ ግፍ እንደ መሆኑ ለምንጊዜዉም በኢትዮጵያ የታሪክ ምዕራፍ ላይ ያረፈ ጥቁር ጠባሳ ሆኖ ይኖራል ። በዚያ አስከፊ ወቅት የአገዛዙን ፈቃድ "ወይድልን "ያሉና በምትኩ ደንበኛ ሕዝባዊ ሥርዐት መተከሉን ግብ ያደረጉ ዜጎች ፡- በሕዝብ መሀከል ሆነዉ ለዚሁ መርህ ታግለዉ ያታገሉ ወገኖች ፡-ከሥቃይም የከፋዉን ሥቃይ እንዲጎነጩ ተደረገ። በየእስር ቤቶቹ ታጎሩ ;- እግሮቻቸዉ እንደ ፓስቲ በዘይት ተጠበሱ ፡-ገላዎቻቸዉ በኤሌክትሪክ ሞገድና በጉማሬ ነፈሩ ;- የእህቶቻችን አካል በዘግናኝና አረመኔያዊ ሁኔታ ተደፈረ፡-የእጅና የእግር ጣት ጥፍሮች በጉጠት ተፈነቀሉ። በዚህም አልበቃ ፡ ባሕልና ትዉፊት ተሽሮ የወገን ሬሣ በየአደባባዩ እንደ ርጥብ እንጨት ተሰጣ ።

በወቅቱ ከነበረዉ ሕዝባዊ ትግል አሰላለፍ አንጻር የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ ) አገሪቱ ካፈራቻቸዉ ምርጥ ምሁራን አብዛኛዉን ከማሰለፉም በላይ የብዙሃኑን ሕዝብ ይበልታና ድጋፍ የተቀዳጀ ነበርና የድርጅቱ መሪዎች ፡-አባላትና ደጋፊዎቹ ከሁሉ የገዘፈዉ የግፍ ድርሻ በላያቸዉ ወድቋል ። ይሁን እንጂ የዚያ የግፍ ዘመቻ ሰለባዎች ኢሕአፓዎች ብቻ አልነበሩም ።የበረንዳ አዳሪዎች ፡-ሀብታም ነጋዴዎች ፡-የጴንጤቆስጤ ሃይማኖተኞች ፡- ወዘተ--- ታስረዋል ፡- ተሰቃይተዋል፡- ተሰድደዋል፡- ተገድለዋል ። ምናልባት ደርግና ገራፊ- ገዳይ - ሎሌዎቹ "ዴሞክራስያዉያን ነበርን " ለማለት የሚቃጣቸዉ ከሆነ በተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ላይ እንበለ-አድልዎ የወሰዱትን "ነጻ ርምጃ " ማስረጃ አድርገዉ መሆን ይኖርበታል። "ቀይ ሽብርን" በሚመለከት "የፍትህ ያለህ " የማለቱ ድርሻ ለኢሕአፓና ለኢሕአፓዎች ብቻ የሚተዉ ሥራ የማይሆነዉም በዚሁ መነሾ ነዉ ። አንድምታዉ በመላዉ አገር ደህንነትና በዜጎች ሁሉ ህይወት ላይ የተፈጸመን አረመኔያዊ ተግባር አጉልቶ የሚያሳይ ነዉ-- "ቀይ- ሽብር "።

አለመታደል ሆነና ፡-የኢትዮጵያ ህዝብ ባደረገዉ ትግልና አተልቆም በከፈለዉ መስዋዕት ወታደራዊዉ ደርግና ስቪል መሳይ የፖለቲካ ድርጅቱ - ኢሠፓ ከሥልጣን ተመንግለዉ አሸባሪዉን አምባገነን በኟሮ በር ካሸሹ በህዋላ የተተካዉ ይብሱኑ ለአገርም ሆነ ለሕዝብ ደህንነት ደንታ የሌለዉ ጎሠኛና ከፋፋይ አገዛዝ ሆነና አረፈዉ ። እንደ ሀገር የምንገኝበት ሁኔታ የሚያዝናናም የሚያጽናናም ከቶ አይደለም -የሚያሰጋ የሚያተጋ እንጂ።

ዛሬም ድብቅና ይፋ እስር ቤቶች በፖለቲካ ዳፋ በታሰሩ እስረኞች ታጭቀዋል ፡፡ ዜጎች በፖለቲካ እምነታቸዉ ዞግ በጠራራ ጸሐይ ይገደላሉ ፡-ይሳደዳሉ-ይሰደዱማል። የሁለቱ አገዛዞች አንጻራዊ ምስያ በዚህ ብቻ አያበቃም ። ትዉልድ ገዳዩን "ቀይ - ሽብር "በተመለከተ ቀዳሚዉና ተከታዩ አገዛዞች ያላቸዉ አቋም በልዩነት ተራርቆ ብዙም አይዘልቅም ። በመሆኑም በነዚያ የጽልመት ዘመናት ለደረሰዉ ጥፋት ተጠያቂዎቹን ከፍትሕ አደባባይ ማቆም አልተቻለም ። ወያኔ በኢሕአፓ ላይ ጦርነት አዉጆ በግንባር የገጠመ ከመሆኑም በላይ መሪዎቹንና ታጋዮቹን ዴት እንዳደረሰ እስከዛሬ ያልገለጸ መሆኑ ይታወቃል ። በመሆኑም ፡-የወያኔ አገዛዝ ለአንድ ሰሞን ዉርዉር ያለበት ሰማዕቱ ያረፉባቸዉን የጅምላ መቃብሮች ቁፋሮ ከታይታ ወዳድ ባህሪዉ የመነጨ ፡-ባልተፈጠረበት "የሰብአዊ መብት አስከባሪነት "ሙከሻ ሊኮፈስ የቃጣበት ግን የጨነገፈበት ሙከራ ከመሆን አልዘለለም ። እንደ ቀድሞዉ ሁሉ፡-አሁንም የኢትዮጵያዉያን ደም ከአራቱም የአገሪቱ ማዕዘናት ለፍትህ እንደጮኸ ነዉ።

በቀደሙት ዘመናት ደርግና ሎሌዎቹ ተቀናጅተዉ ያካኼዱት ሽብርና ፍጅት ቀዳሚ የጥቃት ዒላማዉ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)ና በዙርያዉ ተሰልፈዉ የነበሩ ሀይሎች መሆናቸዉ ርግጠኛ ነዉ ። በአሁኑም ወቅት ይኼዉ ድርጅት የዜጎች እኩልነትና የህግ የበላይነት የሚከበርባት ዴሞክራስያዊት ሀገር ለመፍጠር ከአዲሶቹ አምባገነኖች ጋር በያቅጣጫዉ እየተደረገ ባለዉ ሕዝባዊ ትግል ዉስጥ በመጫወት ላይ የሚገኘዉ ሚና የበኩር ድርሻ ሆኖ መገኘቱ ለወያኔዉ አገዛዝ የስጋትና የቅዠት ምንጭ ሆኗል ።ወያኔዎችና ደርገ-ኢሠፓዉያን በመሀከላቸዉ ተቃርኖ መኖሩን በይፋ ይናገሩት እንጂ ከአፍ ያለፈ ግን ከቶ አይደለም ፡፡ የ"ቀይ- ሽብር"ን ሰቅጣጭ መልክና አዉዳሚ እዉነታ ከመሸፋፈንና በኢሕአፓ ላይ ከሚያደርጉት "ታሪክን አዛባ የመቀባት "ዘመቻ አንጻር በሀልዮና ግብር አንዳቸዉ የሌላኛቸዉ ግብረአበር ናቸዉ ። የትናንቶቹ ነብሰ ገዳዮችና ገራፊዎች አሁን አሁን በሀገር ዉስጥና ዉጭ በሚኖሩት ኢትዮጵያዉያን መሀከል ተመስገዉ ካሉበት ሥፍራ ሁሉ አንገቶቻቸዉን ማቅናት ፡-በማን አለብኝ ባይነት መንጎማለል ጀምረዋል ። በሰማዕቱ ትዉልድ ላይ ከየማዘዣ ወንበሮቻቸዉ ሳሉ በጻፉበትና የ" ግደለዉ-ሰንጥቃት " ቀላጤ በፈረሙበት ብዕር ዛሬ ደግሞ ያንኑ የአረመኔነታቸዉን "ጀብድ " የሚያወድስ "መጽሐፍ "ማሳተም የመጀመራቸዉ መንስዔ ሌላ ምስጢር አይኖረዉም። ባለጊዜዎቹና ጊዜ የጣላቸዉ ግፈኞች የጋራ ባደረጉት "ጠላት "ላይ የሚያደርጉትን ትግግዝና ርብርቦሽ ወደ ተግባር ማሸጋገራቸዉን ብቻ የሚያመላክት ነዉ ።------------(ይቀጥላል )